EARLY STAGES

STRONG BEGINNINGS • BRIGHT FUTURES

# ማህበራዊ ስሜታዊ እድገቶች



## ይህ ማለት ምን ማለት ነው?

ማህበራዊ ስሜታዊ ዕድገት ልጅ እንዴት ስሜቶቹን እንደሚገልጽ፣ ትዕዛዞችን እና ህጎችን እንደሚከተል፣ ግንኙነቶችን እንደሚፈጥር፣ እና በራስ መተማመንን እንደሚገነባ የሚያካትት ነው፡ ፡ የአንድ ልጅ የቤት እና የትምህርት ቤት አካባቢ፣ የህይወት ተሞክሮዎች እና ባዮሎጂ በዚህ አይነት እድገት ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

ፍላጎቶቻቸውን እንዴት እንደሚደግፉ እንዲማሩ ልጅዎን ወደ ነጻ ምርመራ (free screening) ይላኩ!

**ከ0-3 እድሜ፤**

ወደ ስትሮንግ ስታርት **(Strong Start)** ይላኩ

eip.osse.dc.gov

202-727-3665

**ከ3-5 እድሜ፤**

ወደ ኧርሊ ስቴጅስ **(Early Stages)**ይላኩ

www.earlystagesdc.org

202-698-8037

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

## ማህበራዊ ስሜታዊ እድገት በትክክል ሲካሄድ፤ ልጆች የበአብዣኛው ሚከተሉትን ሊያደርጉ ይችላሉ፤

- ክፍል ውስጥ በተሻለ ሁኔታ መማር
- ከሌሎች የዕድሜ አቻልጆች ጋር ጓደኝነት ይመሰርታሉ
- ጠንካራ የንግግር እና ችግር የመፍታት ክህሎቶችን ያዳብራሉ
- በቤት እና በት/ቤት ህጎችን ይከተላሉ
- በፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ በትኩረት ይሰራሉ
- አዲስ ነገሮችን ለመሞከር  በራስ መተማመን ይኖራቸዋል

## ሲዲሲ (CDC) (በሽታዎችን መከላከል እና መቆጣጠር ማዕከል (Centers for Disease Control and Prevention)) የሚከተሉትን የዕድገት ሁኔታዎች ዘርዝሯል፤

### በ2 ወራት፤ አብዛኛ ልጆች...

- ሲናገሯቸው ወይም ፒክ ወደላይ ሲያነሷቸው ረጋ ይላሉ
- ፊትዎን ያያሉ
- ወደነሱ ሲራመዱ ደስተኛ ይሆናሉ
- ሲያዎሯቸው ወይም ፈገግ ሲሉላቸው ፈገግ ይላሉ

### በ 4 ወራት፤ አብዛኛ ልጆች...

- ትኩረትዎን ለመሳብ ፈገግ ይላሉ
- ሊያስቋቸው ሲሞክሩ ፈገግ (ሙሉ ሳቅ ሳይሆን) ይላሉ
- ትኩረትዎን ለማግኘዕጥ ወደርስዎ ያያሉ፤ ይንቀሳቀሳሉ፤ ወይም ድምጽ ያሰማሉ

### በ 6 ወራት፤ አብዛኛ ልጆች...

- የተለመዱ ሰዎችን ያውቃሉ
- በመስታወት ራሳቸውን መመልከት ይወዳሉ
- ይስቃሉ



### በ 9 ወራት፤ አብዛኛ ልጆች...

- በማያውቋቸው ሰዎች አካባቢ አይን አፋር፤ ሙጥኝ ወይም ፈሪ ናቸው
- እንደ መደሰት፤ ማዘን፤ መናደድ፤ እና መገረም የመሳሰሉ በርካታ የፊት ገጽታዎችን ያሳያሉ
- ስማቸውን ሲጠሩ ያያሉ
- ጥለዋቸው ሲሄዱ ምላሽ ይሰጣሉ (ሊደርሱብዎት ይሞክራሉ፤ ወይም ያለቅሳሉ)
- ፒክ ኤ ቡ (peek-a-boo) ሲጫወቱ ፈገግ ይላሉ ወይም ይስቃሉ

### በ 1 ዓመት፤ አብዛኛ ልጆች...

- ፓት ኤ ኬክ (pat-a-cake) የመሳሰሉ ጨዋታዎችን ከእርስዎ ጋር ይጫወታሉ



### በ18 ወራት፤ አብዛኛ ልጆች...

- ከእርስዎ ርቀው ይሄዳሉ፤ ነገር ግን በአቅራቢያ መኖርዎን ለማረጋገጥ ያያሉ
- ያስደሰታቸውን ነገር ለርስዎ ለማሳየት ይጠቁማሉ
- ሲያጥቧቸው እጃቸውን ወደላይ ያደርጉልዎታል
- ከርስዎ ጋር የተወሰኑ የመጽሃፍ ገጾችን ይመለከታሉ
- እጃቸውን በእጅጌ ወስጥ በማስገባት ወይም እግራቸውን በማንሳት ሲያለብሷቸው ያግዙዎታል

### በ 2 ዓመት፤ አብዛኛ ልጆች...

- ሌሎች ሲጎዱ ወይም ሲናደዱ ያውቃሉ፤ሌላ ሰው ሲያለቅስ ዝም ማለት ውይም ማዘን የመሳሰለ
- ለአዲስ ሁኔታ ምን ምላሽ እንደሚሰጡ ለማየት ፊትዎትን ይመለከታሉ

### በ 30 ወራት፤ አብዛኛ ልጆች...

- ከሌሎች ልጆች አጠገብ ይጫወታሉ እና አንዳንድ ጊዜ ከእነሱ ጋር ይጫወታሉ
- “ተመልከተኝ!” በማለት ምን መስራት እንደሚችሉ ያሳዩዎታል
- ሲነገሩ ቀላል አሰራሮችን ይከተላሉ፣ ለምሳሌ “የጽዳት ጊዜ ነው” ሲባሉ አሻንጉሊቶችን ለመውሰድ መርዳት።

### በ 3 ዓመት፤ አብዛኛ ልጆች...

- ከተለዩአቸው በ10 ደቂቃ ውስጥ ይረጋጋሉ፣ ልክ እንደ የህጻን ማቆያ ቦታ
- ሌሎች ልጆችን ያውቃሉ እና አብረዋቸው ይጫወታሉ



### በ 4 ዓመት፤ አብዛኛ ልጆች...

- በጨዋታ ጊዜ ሌላ ነገር ማስመለስ ይችላሉ (መምህር፣ ልዕለ ኃያል፣ ውሻ)
- በአቅራቢያው ከሌለ ከልጆች ጋር ለመጫወት yTeyqaly፣ ለምሳሌ “ከአሌክስ ጋር መጫወት እችላለሁ?”
- የተጎዱ ወይም ያዘኑ ሌሎችን ያጽናናሉ፤ እንደ የሚያለቅስ ጓደኛ የመሳሰሉ
- በመጫወቻ ስፍራው ላይ ከረጅም ከፍታ ላይ እንደ አለመዝለል አይነት አደጋን ያስወግዳሉ
- መርዳት ይወዳሉ
- ባሉበት (የአምልኮ ቦታ፤ ቤተመጻህፍት፤ የመጫወቻ ስፍራ) ላይ በመመስረት ባህሪን ይቀይራሉ



### በ 5 ዓመት፤ አብዛኛ ልጆች...

- ከሌሎች ጋር ጨዋታን ሲጫወቱ ህጎችን ይከተላሉ፤ ተራ ይጠብቃሉ
- ለርስዎ ይዘፍናሉ፤ይደንሳሉ፤ ወይም ይተውናሉ
- በቤት ውስጥ ቀላል የቤት ውስጥ ሥራዎችን፣ ለምሳሌ እንደ ካልሲዎች ማዛመድ ወይም ከተመገቡ በኋላ ጠረጴዛውን ማጽዳት ይሰራሉ